

# ርዕዮት አለሙ እንኳንም ተወለድሽ !



ርዕዮት ...

የልጅ አዋቂ ፣ አርቆ አሳቢ በመሆንሽ
ከግል ቅንጦት ኑሮው ሳያጓጓሽ ፣ ስለፍትህ ብዕር ጨብጠሽ
አድርባይነትን አሽቀንጥረሽ ፣ የእድገት መሰረቱን አመላከትሽ !
ዲሞክራሲያዊ መብት ጥበቃን በተባው ብዕር እያዋዛሽ
እንደ ሻማ ቀልጠሽ እያበራሽ ቀልጠሽ ፣ አንባገነንነትን ተቃወምሽ!

የእኛ ርዕዮት...

ትዳር ጎጆ ሳያጓጓሽ፣ ሃብት ንብረቱ ሳያማልልሽ
ዕዝነ ልቦናሽን ለእኛ ሰጠሽ ፣ሃገርሽን ህዝብሽን አስቀደምሽ
ወጣቷ ስለፍትዕ ርትዕ ስላስተማርሽ በጠባቧ ወህኒ ተከርቸምሽ
በህመም ጻዕር ተቀስፈሽ አለፋ ስቅየትን እየከፈልሽ !
በክብር መኖርን መረጥሽ ፣ አድርባይነትን እንቢ ብለሽ!

ርዕዮት ...
ዛሬን በስቃይ የምትገፊ   ግፉዕ መጻጉዕ በመሆንሽ
የሃገሬ ሰው ያከብርሻል ፣ የሴት አርበኛ በመሆንሽ
ርዕዮት እንኳንም ሰው በጠፋ ቀን ሰው ሆንሽ !
እንኳንም ተወለድሽ  !

አይዞሽ እህታለም ፣
        እነሱ እንጅ አንች አልከሸፍሽም
ትንታጓ መምህር ብዕረኛ ፣
    እኛ እንጅ የቀረብን አንች ከቶ አይቀርብሽም
እኛ እንጅ አንችማ ምን ሆንሽ
          አለም እንደሁ ዝም አላለም ፣

እኛ እንጅ የከሰርን የከሸፍን
       አንች እንደሁ የሴት ብርቱ የእኛ አለኝታ   ጀግናችን ነሽ
የሶስት ጉልቻ ጉጉት የማደግ የመመንደግ አባዜ ሳያጓጓሽ
        እሳት ወላፈኑን ሳትፈሪ ፣ ለእውነት ግንባርሽን የሰጠሽ
አንችማ አንበሳ ነሽ !

በስራሽው ስራ አለም አቀፍን ክብር ያገኘሽ
      ለሃገር ፍቅር ክብር ፣ መስዋዕት የደፈርሽ
ህይወትሽን ለወገንሽ ፍቅር የሰዋሽ አንች እኮነሽ !
      ርዕዮት እንኳንም ተወለድሽ !

ርዕዮት ...

የህልም እንጀራ ያልጠለፈሽ
        ለብሔራዊ ክብርሽ የቀናሽ
ኩሩ ርዕዮት አለሙ አንች እኮ ነሽ
    የኢትዮጵያ ፍቅር የለከፈሽ
የእኛ ድውይ መጻጉዕ ያደረገሽ

ርዕዮት ሰለ እውነት ኖረሻለና ፣
          ዛሬም ነገም ደስ ይበልሽ ፣
ስለ እኛ መጥተሻልና ፣
      ርዕዮት ...እንኳንም ተወለድሽ

እንኳንም ተወለድሽ ፣ አደግሽ
እንኳንም ተማርሽ ፣ ዘመንሽ
እንኳንም ሰብዕናን ፣ አስቀደምሽ
እንኳንም ቀናሽ ፣ ለነጻነትሽ
እንኳንም በብዕር ፣ ታገልሽ
እንኳንም ተናገርሽ ፣ ጻፍሽ
እንኳንም አስተማርሽ ፣  አነቃሽ
እንኳንም ደፈርሽ ፣ አደፋፈርሽ
እንኳንም እግረ ሙቁን ፣ አልፈራሽ
እንኳንም ለኢትዮጵያ ፣ ተሰቃየሽ
እንኳንም አሳር ፍዳሽን ፣ ከፈልሽ
እንኳንም በእሳት ፣ ተፈተንሽ
እንኳንም በቃልሽ ፣ ጸናሽ
እንኳንም መስዋዕትን ፣ አሳየሽ
እንኳንም ከአድማስ አድማስ ፣  አበራሽ
እንኳንም የነጻነት ቀንዲል ሆንሽ !

ስቅየት መከራው ቢበዛም ባንችነትሽ ፣
ለኢትዮጵያስ እንኳንም ተወለድሽ





ነቢዩ ሲራክ
በወህኒ የመከራ ኑሮን ለምትገፋው ጋዜጠኛ ርዕዮት አለሙ መታሰቢያ ተጻፈ !
ጥር 2006 ዓም